# ኢትዮጵያ እና ሱዳን በአዲስ የትብብር ጎዳና

ኢዛና ዘመንፈስ 12/25/13

ለዘመናት  የመላው ኢትዮጵያውያን ህዝቦች ቁጭት ሆኖ የኖረው የዓባይ ወንዝ ለዚች አገር ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም እንዲሰጥ የማድረግ ዓላማ ያለው የኢፌዲሪ መንግስት ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብን መገንባት ከጀመረ እነሆ 3ኛ ዓመቱን ይዟል፡፡

የግድቡ የግንባታ ሒደት አስቀድሞ በታቀደለት ምርሀ ግብር መሰረት እየተከናወነ እንደሆነ ይገኛል፡፡ በዚህ የግንባታ ሂደት ወሳኝ የሚባሉት ተግባራት በሚፈለገው ፍጥነት በመከናወን ላይ እንደሚገኙም ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተሉ ለህዝብ የማሳወቅ ታሪካዊ ሃላፊነት የተጣለባቸው የመንግስት አካላት ከሚሰጡት ማብራሪያ መረዳት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን ከሰሞኑ በጉዳዩ ዙሪያ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሰጡት ቃለ ምልልስ የሚያመለክተውም ይሄንኑ ነባራዊ እውነታ ነው፡፡

“የሕዳሴው ግድብ እንደ የዓይናችን ብሌን የምናየው የህዝባችን ብርቅዬ ሀብት ነው”  ሲሉ መንግስት ለጉዳዩ የሚሰጠውን እጅግ የላቀ ትኩረት ያመለከቱት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የግንባታው ሒደትም አበረታች በሚባል መልኩ ተጠናክሮ መቀጠሉንና ያን ያህልም የሚጋነን እንቅፋት አለማጋጠሙን ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም መሰንበቻውን ከተለያዩ የመንግስትና የግል ሚዲያዎች ተውጣጥተው ግድቡ ወደሚገነባበት ስፍራ የሔዱ ጋዜጠኞች የግንባታ ሒደቱን በዓይናቸው አይተው እንደ መጡና በእርግጥም አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ስለመሆኑ መገንዘባቸውን ነው የዘገቡት፡፡

ይህን እንድል ምክንያት የሆነኝ ደግሞ ባሳለፍነው ህዳር ወር መገባደጃ ላይ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን ጨምሮ የግል ፕሬሶችን ባካተተ መልኩ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ወደሚገነባበት የዓባይ ወንዝ ምእራባዊ ዳርቻ የተጓዙ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች

የግድቡ ግንባታ ሒደት የሚገኝበትን ተጨባጭ እውነታ እየተዘዋወሩ ተመልክተው ያቀረቡዋቸውን ዘገባዎችና ሃተታዎች ማንበቤ ነው፡፡

ለአብነት ያህል የሰንደቁ ጋዜጠኛ ዘሪሁን ሙሉጌታ "ሁለት ሰዓታትን በህዳሴው ግድብ" የሚል ርእስ የሰጠውንና በዓይኑ ከተመለከተው እውነታ በመነሳት ያጠናቀረውን ሪፖርታ» ታህሣሥ ሁለት ቀን 2006 ዓ.ም ታትሞ በወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ማስነበቡን ማስታወስ የሚበቃ ይመስለኛል፡፡

ለነገሩ ሌሎቹም የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ከጉብኝቱ መልስ ያጠናቀሩትን ዘገባ በየራሳቸው የሚዳያ ተቋም አማካኝነት ወደ ህዝብ ማድረሳቸውን በእርግጠኝነት ለመናገር እችላለሁ፡፡

የሁሉም ወገኖች ምስክርነት ሲጠቃለልም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ የግንባታ ሒደቱ እጅግ በሚያስተማምን ሁኔታ እየተከናወነ እንደሚገኝና በታቀደለት መልኩ ዳር ለማድረስ ርብርቡ ይበልጥ ተጠናክሮ እንደቀጠለ የሚያረጋግጥ ድምር ውጤት ላይ ያደርሰናል የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡

እንግዲህ ከዚህ አኳያ ስንመለከተው ጤናማ ይዘት ባለው የግንባታ ሒደት ላይ የሚገኘውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በተመለከተ የዓባይ ተፋሰስ አገራት ከትላንት እስከ ዛሬ ያሳዩትን አቋምና በዚህ ረገድም ሱዳናውያኑ ወንድሞቻችን የያዙት ቀና መንገድ ለሌሎች የተፋሰሱ አባል ሀገራት ጭምር አርአያነቱ የጎላ ስለመሆኑ አንስተን ጥቂት እንጨዋወት ዘንድ መልካም መሰሎ ቢታየኝ ነው ብዕር ማንሳቴ ፡፡

በተለይም ሰሞኑን ሀገራችን በዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ስላለችው ግዙፍ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ዘላቂ እጣ - ፈንታ ለመምከር ኢትዮጵያ ሱዳንና ግብፅ ካርቱም ላይ ተገናኝተው የሶስትዮሽ ውይይት አካሂደዋል፡፡ በዘዘዘዚህ ውይይት ላይ የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኡመር ሐሰን አልበሽር እጅግ በጣም ጠቃሚና ገንቢ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ ይህ የአልበሽር መልእክት ከግብፆች በኩል ለጉዳዩ ከሚሰጠው የተንሸዋረረ ትርጉም ጋር ሲነፃፀር ሱዳናውያን ወንድሞቻችን የዓባይ ተፋሰስን የውሃ ሀብት ለሁሉም የባለድርሻ ሀገራት ህዝቦች የጋራ ጥቅም የማዋል ፍትሐዊ ስምምነትን በማስቀጠል ረገድ የማይናወጥ አቋምና ግልፅነት የተላበሰ መርህ እንዳላቸው የሚያመለክት ሆኖ ተሰምቶኛል፡፡

እንደኔ እምነት ከሆነ የሱዳን ህዝብና መንግስት በተለይም ሶስቱን የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት (ኢትዮጵያን፣ ግብፅንና ራሷን ሱዳንን) ያማከለ መግባባት መፍጠር ምን ያህል አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ከመቸውም ጊዜ በላይ ግልፅ ያደረጉበት መልካም አጋጣሚ ነበር ማለት ይቻላል፤ የሰሞኑ ውይይት፡፡

የአልበሽር አቋም የዓባይ ወንዝ መነሻ ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች ሰማኒያ አምስት በመቶውን የውሃ መጠን በምታዋጣበት የናይል ተፋሰስ ተፈጥሯዊ ፀጋ የበይተመልካች ሆና መኖሯ አልበቃ ብሎ፣ ዛሬም ድረስ ያው የቅኝ ግዛት ዘመን ኢ - ፍትሐዊ ስምምነት እንዲቀጥል ለሚሹ አንዳንድ ግብፃውያን ፖለቲከኞች ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ቁጥርጠኝነት ተንፀባርቆበታል፡፡

ሱዳን የያዘችው በመርህ ላይ የተመሰረተ ፅኑ አቋም፣ በየአጋጣሚው አገራችን ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባውን የህዳሴ ሃይል ማመንጫ ግድብ ለታችኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት (ለሱዳንና ለግብፅ) ህለውና የማይበጅ አደጋ የሚጋርጥ አስመስለው እያናፈሱ ህዝባቸውን ለማደነጋገር ሲሞክሩ ለሚስተዋሉ አንዳንድ የግብፅ ምሁራንና የነሱን ያረጀ ያፈጀ አስተሳሰብ እንደወረደ ተቀብለው በማዘመት ረገድ የሚታወቁት የአረቡ ዓለም ሚዲያዎች ወደ አእምሯቸው ተመልሰው ለሀገራቱ ዘላቂ ጥቅም የተቀየሰውን ቀና መንገድ እንዲመለከቱ የሚያነቃ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚሁ ጋር አብሮ መነሳት ያለበት ሌላው ቁልፍ ጉዳይ፣ ሱዳናውያኑ ወንድሞቻችን ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ መገንባቷ የተፋሰሱን የግርጌ ሀገራት ጭምር ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ ማንንም የሚጎዳ እንዳለሆነ ሽንጣቸውን ገትረው በመከራከር ላይ ያሉት ከግብፅ መንግስትና እንዲሁም ፈርኦናዊ አመለካከት ከተጠናወታቸው ግብፃውያን ልሒቃን ሊሰነዘርባቸው የሚችለውን ተፅእኖ ተቋቁመው መሆኑ ነው፡፡

ግብፃውያን ፖለቲከኞች ከዚህ ቀደም ሱዳን በዓባይ ዙሪያ እነሱ የሚያራምዱትን ግትር አቋም ከመደገፍ ያለፈ ሚና እንዳይኖራት ለማድረግ የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ ታክቲኮችን ተጠቀመዋል፡፡ ከእነዚህ መሃከል ሀገራቸው ግብፅ የአረብ ሊግ መስራችና የእንቅስቃሴው መሪ ተዋናይ መሆኗን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመው ሱዳናውያኑን የዓረቡ ዓለም ብሔረተኝነት አካል የማድረግ እንዲሁም በሙስሊም ወንድማማችነት ሽፋን ሱዳንን የሊጉ

አባል ማድረግና ከዚሁ ሃይማኖታዊ ወገንተኝነት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ እንዲጠመዱ የማድረግን ጥረት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ "ጊዜ ለኩሉ" እንዲል መፀሐፊ ጠቢብ እነሆ ዛሬ ላይ ያን ዓይነቱን ያረጀ ያፈጀ ዲፕሎማሲያዊ ታክቲክ በመጠቀም የሱዳንን ህዝብና መንግስት ለግብፃውያን ኢ-ፍትሐዊነት የተጠናወተው ውሳኔ እንዲገዙ የሚያደርግ ተፅእኖ ማሳደር የሚቻል አልሆነም፡፡

ይህ አሁን የምንገኝበት 21ኛው ክፍለ ዘመን የ" አንተ አብራ እኔ ልብላ" ዓይነት ፍርደገምድልነት ጎልቶ ለተገለፀበት እኤአ የ19 29 እና የ1959 ዓ/ም ኢ- የፍትአዊ የውሃ አጠቃቀም ስምምነት ቦታ የሚሰጥ አየደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ በሰለጠነ አስተሳሰብ ላይ ተመስርቶ በሚደረግ ውይይት የሁሉንም ባለድርሻ ሀገራት የጋራ ጥቅም ሊያረጋግጥ የሚችል ዘላቂ የመፍትሔ አቅጣጫ መቀየስን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም የሱዳኑ ፕሬዚዳንት የተከበሩ ዑመር ሐሰን አልበሽርና መንግስታቸው ያሳዩት ቁርጠኝነት ተገቢነቱ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ይልቁንስ ዛሬም ድረስ የዘመነ ቅኝ አገዛዝን ቅጥ ያጣ ኢ-ፍትሐዊነት መሰረት አድርጎ በእንግሊዛውያን ቅኝ ገዡዎቻቸው የተፃፈውን ያረጀ - ያፈጀ ውል እንደፈጣሪ ቃል ሊቆጥሩት የሚቃጣቸው የግብፅ ምሁራንና ፖለቲከኞችም ከሱዳን መንግስት በመርህ ላይ የተመሠረተ ፅኑ አቋም ብዙ ቁም ነገር ሊማሩበት የሚገባ ይመስለኛል፤ በግሌ፡፡

በተረፈ ግን ሀገራችን አሁን በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባው የታላቁ የህዳሴ ሃይል ማመንጫ ግድብ ስራው ከተጀመረ አንብስቶ ሱዳናውያን ምሁራን ዜጎችና መንግስታቸው ያሳዩት ቀና ትብብር ግንባር ቀደም የልማታችን አጋሮች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሆኖ እንዳገኘሁት በዚህ አጋጣሚ ሳልገልጽ ማለፍ አይኖርብኝም፡፡ እንደኔ መረዳት ከሆነም በኢትዮጵያና በሱዳን ህዝቦች የጉርብትና ታሪክ እጅግ መልካም ሊባል የሚችለው አዲስ ምእራፍ እንደተከፈተ ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡

ምንም እንኳን መጭው ዘመን ለሁሉም የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ከመቼውም ጊዜ በላይ በጠነከረ መልካም ጉርብትና እየኖሩ የጋራ እድገትና ብልፅግናን ለመቀዳጀት የሚያስችላቸውን ብሩህ ተስፋ የሰነቀ ስለመሆኑ ከወዲሁ መገመት ባያዳግት የሱዳንና የኢትዮጵያ ህዝቦች ወንድማማችነት በተለየ መልኩ እያደገ እንደሚገኝና ምናልባትም

ወደፊት የመላው አፍሪካውያንን ህዳሴ በማፋጠን ረገድ ዓይነተኛ ምሳሌ ለመሆን ወደሚያስችለው ደረጃ የማይደርስበት ምክንያት እንደማይኖር ይሰማኛል፡፡

ይህ የኔ ግምት ከባዶ ምኞት የመነጨ ፖለቲካዊ ስሌት የሚመስለው እንባቢ ካለ ደግሞ በተለይም ለኢትዮ - ሱዳን አዲስ የትብብር ምዕራፍ ይከፍታል ተብሎ የሚጠበቀውንና በሱዳኗ የድንበር ከተማ በገዳሪፍ እንዲካሔድ የተወሰነው የሁለትዮሽ ስብሰባ ውጤት ከወዲሁ ለመተንበይ የሚያስችሉ ሰሞነኛ መረጃዎችን ይመለከት ዘንድ እየጋበዝኩኝ ለሁለቱ የዓባይ ተፋሰስ ባለድረሻ ሀገራት ወንድማማች ህዝቦች መልካም ጉርብትና ተጠናክሮ መቀጠል ያለኝን ልባዊ ድጋፍ ለመግለፅ ያህል የጫጫትርኳትን ጽሁፌን እዚህ ላይ ማጠቃለሌ ነው፡፡